ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር
በየሳምንቱ ሰኞና ዓርብ የሚታተም

# ብሔራዊ ፈተና እንዴት አለፈ?

ቤዛ እሸቱ


ከጥቅምት 29 እስከ ኅዳር 2 የተካሄደው እና ከስድስት መቶ ሺ በላይ ተማሪዎች የተፈተኑበት የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና እንዴት ተካሄደ? በማለት በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ተዘዋውረን ለመቃኘት ሞክረናል፡፡ በዚህም የተለያዩ አካላትን ሀሳብ አሰናድተን አቅርበንላችኋል፡፡

**የክላስተር አስተባባሪዎች እና ርዕሰ መምህራን**

የሞጆ ክላስተር አስተባባሪ የሆኑት አቶ ተሾመ ነጋሽ፣ በክላስተሩ 25 የመፈተኛ ማዕከላት መኖራቸውን እና በዚህም 7,292 ተማሪዎች ፈተና መውሰዳቸውን ተናግረዋል፡፡ ፈተናው ከመጀመሩ በፊት ለተፈታኝ ተማሪዎች፣ ለፈታኝ መምህራን እና ለአስተባባሪዎች ስልጠና መሰጠቱን ገልጸው፤ አስተባባሪዎቹ በየመፈተኛ ማዕከላቱ በመሄድ ፈተና ለመፈተን የሚያስችል ሁኔታ ላይ መሆናቸውን አረጋግጠው በመጀመሩ ፈተናው ያለምንም ችግር መጠናቀቁን ገልጸዋል፡፡

በስሩ 20 የመፈተኛ ጣቢያዎችን ያቀፈው የአዳማ ክላስተር አስተባባሪ አቶ ለሚ ለታ የፈተና ቀናቸው ሲቃረብ የወለደች እና አንድ የቀዶ ሕክምና ያደረገ ተማሪ ከመኖራቸው በስተቀር ምንም ያጋጠመ ችግር አለመፈጠሩን ጠቅሰዋል፡፡ ለእነርሱም ፈታኝ ተመድቦ ለብቻቸው የሚፈተኑበት ሁኔታ መመቻቸቱን ገልጸዋል፡፡ በሌላ በኩል የተወሰኑ ተማሪዎች የሞባይል ስልክ ይዘው ለመግባት ቢሞክሩም በር ላይ ባለው ጥብቅ ፍተሻ የያዙት የሞባይል ስልክ በመመለሱ ፈተናው በሰላም መጠናቀቁን ገልጸዋል፡፡

በ2012 ዓ.ም በነበረው አገር አቀፍ ፈተና አራት ተማሪዎች ከ600 በላይ ያመጡበት የቢሾፍቱ ከፍተኛ መሰናዶ ትምህርት ቤት ምክትል ርዕሰ መምህር አቶ አብዲሳ አባቡ፣ 1,495 የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች እና 152 የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች በትምህርት ቤቱ ፈተናውን ያለምንም ችግር መውሰዳቸውን ገልጸዋል፡፡ ትምህርት ቤቱ በኩረጃ ዙሪያ ምህረት የሌለው መሆኑን፤ ከዚህ ቀደም



በትምህርት ቤቱ በሚሰጡ ፈተናዎች ሲኮርጅ የሚያዝ ተማሪ ለፈተናው ዜሮ ስለሚሰጥ እና ይሄንንም ተማሪዎቹ ስለሚያውቁት ተዘጋጅተው የየራሳቸውን የመስራት ባህል እንዲኖራቸው ማድረጉን ተናግረዋል፡፡ ተማሪዎቹ ከባለፈው ዓመት የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግቡ የማዘጋጀት ሥራ ሢሰሩ እንደነበር እና በዚህም የተሻለ ውጤት እንደሚጠብቁ ገልጸዋል፡፡

**የተፈታኝ ተማሪዎች አስተያየት**

በአዳማ ሞዴል ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከፈተና ስትወጣ ያገኘናት ተማሪ ሀናን ሙስጠፋ፣ በዚህ ወቅት የማኅበራዊ ትስስር ገጾች መዘጋታቸው ተማሪዎች ሀሳባቸውን ፈተናው ላይ አተኩረው እንዲሰሩ እንዳገዛቸው ትገልጻለች፡፡ ከዚህ ቀደም ፈተናው ወጥቷል የሚለው ሀሳብ በራሱ የተዘጋጀውንም ተማሪ ወደ ጭንቀት ስለሚከተው በውጤት ላይ ተጽዕኖ እንደሚያመጣ ተናግራለች፡፡ አሁን ግን የማኅበራዊ ትስስር ገጹ ለተወሰነ ቀን በመቋረጡ ከመረበሽ ነጻ ሆና ፈተናውን መውሰዷን እና ጥሩ ውጤት እንደምትጠብቅ ገልጻለች፡፡

በትምህርት ማብቂያ እና በፈተናው መሐል ረዥም እረፍት መኖሩ በተወሰኑ ተማሪዎች ላይ መዘናጋት መፍጠሩን እና በደብረብርሃን ከተማ የሚሊኒየም ትምህርት ቤት ተማሪ ሆና ወደ ኃይለማርያም ማሞ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለፈተና ስትገባ ያገኘናት ተማሪ ትንቢተ ኤልያስ ናት፡፡ ትምህርቱ ቢጠናቀቅም ቤተ መጽሐፍት ክፍት በመሆኑ ያነቡ እንደነበር እና ያልገባቸው ነገር ሲኖር አስተማሪዎቻቸውን ይጠይቁ እንደነበር ትናገራለች፡፡ በተለይ ከአካባቢው ርቀት ላይ ችግር ስላለ ፈተናው ላይሰጥ ይችላል የሚል ስጋት በተማሪው ውስጥ እንደነበር፤ ነገር ግን በከተማው የሚገኘው የትምህርት ማኅበረሰብ በገለጻ (ኦረንቴሽን) ወቅት ምንም ችግር እንደሌለ እና የተጠናከረ የጸጥታ ኃይል እንዳለ በመንገራቸው እና በተግባርም ስላዩችው መረጋጋቷን ትገልጻለች፡፡ ፈተናው ሰዓቱን ጠብቆ መከናወኑን እና ሁሉም የየራሱን የሠራ መሆኑን ገልጻለች፡፡

**በተለዩ አጋጣሚዎች ውስጥ ሆነው የተፈተኑ ተማሪዎች**

ተማሪ በረከት ተስፋዬ፣ የተሻለ ውጤትን ለማምጣት በማሰብ ያለረፍት አንድ ቦታ በመቀመጥ ረጅም ጊዜ ሲያነብና እዚያው ሲመገብ የነበረ ነው፡፡ ፈተናው ሰኞ ሊጀመር ከቅዳሜ ጀምሮ ከፍ ያለ ሕመም ሲሰማውም እንደነበር አውግቶና፡፡ እሁድ ጠዋት ህመሙን መቋቋም ስላልቻለ ወደ ሆስፒታል ያመራ ሲሆን፣ በወቅቱም ትርፍ አንጀት እንደሆነ እና በአስቸኳይ የቀዶ ሕክምና እንደሚያስፈልገው ስለተነገረው ሕክምናውን አከናውኗል፡፡ ሰኞ እለት በቀዶ ጥገናው ማግስት ፈተናውን እንዳይወስድ እና ለቀጣይ ዓመት ድጋሚ እንዲወስድ እንደሚያመቻቹለት አስተማሪዎቹ እና ቤተሰቦቹ ሀሳብ ቢያቀርቡም፤ እርሱ ግን ፍቃደኛ አልሆነም፡፡ በወቅቱ የሰጠው ምላሽ ‹‹ጊዜ ሰጥቼ ስላነበብኩና ስለተዘጋጀሁ መፈተን አለብኝ!›› ነበር ፡፡ እኛም ከሚድያ ባለሙያዎች ጋር በትምህርት ቤቱ የመስክ ምልከታ ባደረግንበት ወቅት ለብቻው ፈታኝ ተመድቦለት ሲፈተን ተመልክተናል፡፡

የትምህርት ቤቱ ማኅበረሰብ የተመቻቸ የመፈተኛ ቦታ እንዲያገኝ ስለተባበሩት እንደሚያመሰግን ገልጾ፤ ከዚህ ቀደም በነበሩ አገር አቀፍ ፈተናዎች ወልደው እና የተለያየ አደጋ ደርሶባቸው ሲፈተኑ የነበሩ ሰዎችን ማየቱ እንዳበረታው ሐሳቡን አካፍሎናል

በተመሳሳይ ፈተናው አንድ ቀን ሲቀረው በደብረብርሃን ከተማ የሚገኘው ኃይለማርያም ማሞ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ የወለደች ቢሆንም፤ የመጀመሪያው ሁለት ቀናት ለብቻዋ ፈታኝ ተመድቦላት ፈተናውን ወስዳለች፡፡ ቀሪውን ሁለት ቀናት ከጓደኞቼ ጋር ተቀላቅዬ መፈተን እችላለሁ ስላለች አብራ በመፈተኛ ክፍሏ ውስጥ ተፈትናለች፡፡ ሌላም ፈተናው ሁለት ቀን ሲቀረው የወለደች ተማሪ በአዳማ ለብቻዋ መፈተኛ ክፍል ተዘጋጅቶላት መፈተኗን ለማወቅ ተችሏል፡፡

የአገር አቀፍ የትምህርት ምዘና እና ፈተናዎች ኤጀንሲ የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ረዲ ሺፋ፣ በአካባቢያቸው ባለ የጸጥታ ችግር መፈተን ያልቻሉ በአማራ አንዳንድ አካባቢዎች ማለትም ሰሜን ወሎ፣ ደቡብ ወሎ፣ ዋግህምራ፣ ኦሮሞ ብሄረሰብ አስተዳደር ዞን፣ ሰሜን ጎንደር ውስጥ፤ ጠለምት፣ አዳርቃይ፣ ሰሜን ሸዋ የሚገኙ አጣዬ፣ ግሽርአባሌ፣ ኤፍራታና ግድም፣ አንጾኪያ በሚገኙ 131 የፈተና ጣቢያዎች ይፈተኑ የነበሩ 36 ሺ 340 ተማሪዎች በቅርቡ በሚወጣ ሁለተኛ ዙር መርሐ ግብር የሚፈተኑ ይሆናል ብለዋል፡፡

ከፐብሊክ ሰርቪስ የሰራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ጋር
በመተባበር በየ15 ቀኑ ዓርብ የሚታተም

# ‹‹የድርጅቱ የውጤት መሠረት ቅንጅታዊ ሥራ ነው››

**ወይዘሮ አየለች ጫሚሶ**
**የቀድሞ የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታና የድርጅቱ ቦርድ አባል**

ፐብሊክ ሰርቪስ የሠራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ወደ ሥራ ከገባ በኋላ ከመንግሥት ሠራተኛው ባሻገር ለነዋሪውም የታክሲ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። በየጊዜውም ዘመናዊ አሠራሮችን በመከተል ለሌሎች ተቋማት አርዓያ እየሆነ ይገኛል። የቀድሞ የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታና የድርጅቱ ቦርድ አባል የሆኑት ወይዘሮ አየለች ጫሚሶ ጋር ስለ ድርጅቱ የሥራ እንቅስቃሴ የተደረገውን ቆይታ በሚከተለው መልኩ አቅርበነዋል።

**ፐብሊክ ሰርቪስ፡-ፐብሊክ ሰርቪስ ለሠራተኛው የሚሰጠውን አገልግሎት እንዴት ያዩታል?**

**ወይዘሮ አየለች፡-** ድርጅቱ ተቋቁሞ አገልግሎት መስጠት ከጀመረበት 2007 ዓ.ም ጀምሮ እስካሁን የተጓዘበትን የዕድገት ደረጃ ስንመለከት በርካታ ስኬቶች እያስመዘገበ በስኬት ላይ ስኬትን እየደረበ በመሄድ ላይ ያለ ድርጅት ነው ለማለት እደፍራለሁ። በተለይ ድርጅቱ የተሰጠው በአዲስ አበባ ደረጃ ቢሆንም አገልግሎቱን ተደራሽ ለማድረግና የብዙዎችን የቆየ ጥያቄ በመመለስ ረገድ በአዲስ አበባ ዙሪያ ላሉ የኦሮሚያ ከተሞች አገልግሎት መስጠት መጀመሩ እጅግ ስኬታማና ውጤታማ አድርጎታል።

ይህ ውጤት እንዴት መጣ ብሎ መጠየቅ ተገቢ ይሆናል። ውጤት፣ ምኞትና ፍላጎት ስላለ ብቻ የሚመጣ አይደለም፤ በልፋትና በድካም እንጂ። ያለድካም የሚገኝ ውጤት ጊዜያዊና ፈራሽ ነው ። የሆነ ነገር ሲነካው



የሚሟሽሽ ይሆናል። በድካም፣ በጥረትና በመስዋዕትነት የሚገኝ ውጤት ግን ሁሌም ያኮራል፤ የማይገረሰስና የማይናወጥ መሠረት ላይ የፀና ይሆናል። የፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት የውጤት መሠረትም ቅንጅታዊ ስራ ነው። ሠራተኛውና አመራሩ በአንድ እጅ ተያይዞ፤ በአንድ ልብ ተቀናጅቶ፤ በአንድ ዓላማ በመሥራቱ ነው ውጤቱ ሊመዘገብ የቻለው። ኃላፊነትን ተገንዝቦና አውቆ ለአገርና ለሕዝብ ተቆርቋሪ ሆኖ መሥራትም ይጠይቃል። ይህ በመሆኑ በአጭር ጊዜ ድርጅቱ በርካታ ውጤቶችን ሊያስመዘግብ ችሏል። በቀጣይም ለብዙ ተቋማት አርአያ የሆነ ተግባራትን እንደሚያስመዘግብ ባለ ሙሉ እምነት ነኝ።

**ፐብሊክ ሰርቪስ፡- የመንገድ ላይ የትራፊክ አደጋ ለመከላከል ድርጅቱ እያደረገ ያለን ጥረት እንዴት ያዩታል?**

**ወይዘሮ አየለች፡-** አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ማሽከርከር ከባድ እንደሆነ ለመረዳት የግድ አሽከርካሪ መሆን አይጠበቅም፤ መንገዱ ካለመመቸቱ ባሻገር የአሽከርካሪዎች ሥነ ምግባር እጅግ ፈተና ነው ። ለዚህም ነው በየቀኑ የሰው ሕይወት በቀላሉ በአደጋ የሚያልፈው። አደጋን ተከላክሎ ማሽከርከር ይቻላል ብሎ የፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት በመነሳቱ በእርግጥም አደጋን ለመከላከል እንደሚቻል አሳይቷል። ቅጣት አስተማሪ ሊሆን ይችላል። ግን ድርጅቱ ከቅጣት በፊት ሽልማትን ያስቀደመ ድርጅት ነው። ሁሌም በየዓመቱ ምንም ዓይነት የተሽከርካሪ አደጋ ያላደረሱ ባስ ካፒቴኖችን በክብር ይሸልማል። ይህ ቅጣት ከመቅጣት ይልቅ አስተማሪ ነው።

አደጋ ደርሶባቸው ሆነ አድርሰው ያልተሸለሙት በቀጣይ ተሸላሚ ለመሆን ከፍተኛ ጥረት ሲያደርጉ ታይተዋል። ይህ አደጋን ለመከላከል ድርጅቱ የተገበረው ስትራቴጂ ነው። ደሞ የተሳካ ነው። ሁሌም በየዓመቱ ታላቅ ሥነ ሥርዓት ተደርጎ ለተከታታይ ዓመታት አደጋ ሳያደርሱ የተሸለሙ ባስ ካፒቴኖችን መመልከት በጣም አስደሳች ነው። ሌሎች ተቋማትም ይህን ልምድ ቢያዳብሩ መልካም ነው። ያጠፋውን ከመቅጣት ያላጠፋውን መሸለም ይበልጥ አስተማሪ ነው ብዬ አምናለሁ። ሁሉም ተቋማት በተለይ የሕዝብ ትራንስፖርት የሚሰጡ የትራንስፖርት ተቋማት ይህን ቢተገብሩ እንደ አገር በድምሩ አደጋው ሊቀንስ ይችላል። በአጠቃላይ ድርጅቱ ያገኘው የጥራት ሽልማት ሲያንስበት እንጂ አይበዛበትም። እንደ ቦርድ የሠራተኞቹንና አመራሩን ሥራ ትጋት በቅርበት ስለምናውቅ መሸለማቸው ትክክል ነው። በዚህ አጋጣሚ ለሚሸለሙ ሠራተኞችና የማኔጅመንት አባላት እንኳን ደስ ያላችሁ ቀጣዩ ስራ ዘመን የተሻለ ውጤት ይሁን እላለሁ።

**ፐብሊክ ሰርቪስ፡- ለሌሎች ተቋማትም ምርጥ ተሞክሮ የሚሆን አሠራር አለ ይላሉ ?**

**ወይዘሮ አየለች፡-** ብዙ የድርጅቱ ሥራዎች ለተሞክሮ የሚቀመሩ ናቸው። የድርጅቱ ማኔጅመንቱና ሠራተኛው ተግባብተው የሚሰሩበት መንገድ አስደሳች ነው። በብዙ ቦታ ይሄ አይታይም። መግባባት ካለ ውጤት አለ። አንድነት ካለ ድል አለ። በአንፃሩ ደግሞ መግባባትና አንድነት ከሌለ በአንድ ሥራ ለአንድ ዓላማ መቆም አይቻልም። በፋንታው ፀብና ጭቅጭቅ ይጎለብታል። ተግባብቶ መሥራት እንደ በጎ ተሞክሮ ሊወሰድ የሚችል የድርጅቱ እሴት ነው።

ሠራተኛው ያለምንም ጎትጓችና አለቃ ጥበቃ በራሱ ተነሳሽነት ኃላፊነቱን እንዲወጣ ነው የሚያደርገው። ከዚህ ባለፈ ግን በየጊዜው የክትትልና የቁጥጥር ሥራው ተጠቃሽ ነው። ማኔጅመንቱ ራሱ በየስፍራው በመንቀሳቀስ ያለውን የሥራ ሁኔታ ይቃኛል፤ ይገመግማል። የሚያየው ክፍተት ካለ እዚያው የማስተካከያ ርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል።